# ስሙም ድንቅ ይባላል

በኬኔት ኢ.. ሄገን

# ስሙም ድንቅ ይባላል

His Name Shall Be Called Wonderful

በኬነት ኢ. ሄገን
By Keneth E. Hagin

## ምዕራፍ ፩

## ስሙ ድንቅ ነው

*ኢሳይያስ 9:6፤ ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።*

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፥ ኢሳይያስ በያሑዋሕ መንፈስ (በእግዚአብሔር መንፈስ)፥ ስለኢየሱስ ልደት፥ የሚመጣው መሢሕ፥ ትንቢት እየተናገረ ነበር። "ስሙ ድንቅ ይባላል" በሚለው ጥቅስ አንድ ወይም ሁለት ስብከቶችን መስበክ ይቻላል፥ ከዚያ ደግሞ "መካር"፥ "ኃያል" በሚሉት ደግሞ ሌሎች ብዙ። እውነታው፥ በእነዚህ ጥቅሶች ለዘላለም መስበክ ይቻላል።

ያሑዋሕ ይመስገን፥ ኢየሱስ ሁሉንም ነው እንዲያውም ከዚያም በላይ ነው! በዚህ መልዕክት "ስሙም ድንቅ ይባላል" የሚለውን ጥቅስ እንመለከታለን።

የገና ጊዜ፥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እውቅና እንሰጣለን። ሆኖም ግን፥ ልደቱ ምንም ባይኖረው - ተወልዶ እዛው ቢያልቅ - ምንም የመዳን እቅድ አይኖርም።

እስቲ የያሑዋሕን እቅድ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እንመልከት፦

በእርግጥም እርሱ ድንቅ ነው።

በእርግጥም መጸነሱ ድንቅ ነበር።

የልጅነት ጊዜው ድንቅ ነበር።

በአገልግሎት ድንቅ ነበር።

በሞቱ ድንቅ ነበር።

በትንሣኤው ድንቅ ነበር።

እንዲሁም፥ ያሑዋሕ ይመስገንና፥ በዳግም መምጣቱም ድንቅ ይሆናል።

ይሄ ሁሉ ከገና ታሪክ ጋር ተያይዞ ሊታይ ይችላል። ጥቅሶቹ ለራሳቸው እንዲናገሩ እንተዋቸዋለን።

መጀመሪያ፥ መጸነሱና የመወለዱ ብስራት ድንቅ ነበር። ሁሉም የወንጌሉ ጸሐፊዎች ታሪኩን ዘግበውታል፥ ነገር ግን ሉቃስ ትንሽ ጠለቅ ብሎ ይገባል፥ በመሆኑም የበለጠ የእርሱን ምስክርነት እወደዋለሁ፥

ሉቃ1:26-37
26 በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፥
27 ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።
28 መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ። ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት።
29 እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና። ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች።
30 መልአኩም እንዲህ አላት። ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ።
31 እነሆም፥ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።
32 እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤
33 በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።
34 ማርያምም መልአኩን። ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።
35 መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።
36 እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤
37 ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።

ኢየሱስ እንደሚወለድ ብስራቱ ድንቅ ነበር - መልአክ ሊያበስር መጣ!

በተጨማሪም፥ መጸነሱ ድንቅ ነበር። ማርያም አንዲት ድንግል እንዴት ልትጸንስና ልትወልድ ትችላለች ብላ እየጠየቀች ነበር። "መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።" (ቁጥር 35)

ሉቃስ 1፡38-40

38 ማርያምም። እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ።
39 ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች፥
40 ወደ ዘካርያስም ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት።

ሉቃስ በምዕራፍ ሁለት ላይ እንደጠቀሰው፥ ማርያም ስለመልአኩ ጉብኝት ለማንም አልተናገረችም፤ ብቻ ግን የተናገራትን በልቧ ታስበው ነበር። ስለዚህም፥ ዘመዷ ኤልሳቤጥ ትንቢት መናገር በጀመረችበት ጊዜ በማርያም ምን እንደተከሰተ አታውቅም ነበር። ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ ነበር ትናገር የነበረው።

ሉቃስ 1፡41-56
41 ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፥
42 በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።
43 የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?
44 እነሆ፥ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና።
45 ከጌታ፤ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት።
46 ማርያምም እንዲህ አለች።
47 ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤
48 የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤
49 ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው።
50 ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል።
51 በክንዱ ኃይል አድርጎአል፤ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል፤
52 ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል፤
53 የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል፤ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል።
54-55 ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ፥ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል።
56 ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል በእርስዋ ዘንድ ተቀመጠች ወደ ቤትዋም ተመለሰች።

ኢየሱስ እንዴት እንደሚወለድና እንደሚጸነስ ያለው ብስራት ድንቅ የሚለው ቃል እንዴት እንደሚሠራለት እናያለን።

ጥቅሶቹን መለስ ብለን እየተመለከትን የያሑዋሕ ቃል የመወለዱን ብስራት ታሪክ እንዲገልጸው እንተዋለን።

ሉቃስ 2፡1-20
1 በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች።
2 ቄሬኔዎስ በሶርያ አገር ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፈት ሆነ።
3 ሁሉም እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ።
4-5 ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ፥ ፀንሳ ከነበረች ከእጮኛው ከማርያም ጋር ይጻፍ ዘንድ ወጣ።

6 በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፥
7 የበኵር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ስፍራ
ስላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።
8 በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ።[አሁን፥
አስተውሉ፤]
9 እነሆም፥ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፥ ታላቅ
ፍርሃትም ፈሩ።

መልአኩ ለእነርሱ መገለጥ ብቻ አይደለም፥ የያሑዋሕም ክብር በዙሪያቸው አበራ ይላል። ያው ተመሳሳይ ክብር በብሉይ ኪዳን ሙሉ ሲገለጽ ነበር፤ ብዙ ጊዜ እንደ ደመና፥ አንዳንዴ ደግሞ እንደ ደማቅ፥ የሚያበራ ብርሃን።

10 መልአኩም እንዲህ አላቸው። እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች
እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤
11 ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።
12 ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፤ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግምም ተኝቶ ታገኛላችሁ።
13 ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ። እግዚአብሔርንም
እያመሰገኑ።
14 ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።
15 መላእክትም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ፥ እረኞቹ እርስ በርሳቸው።
እንግዲህ እስከ ቤተልሔም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን
ነገር እንይ ተባባሉ።
16 ፈጥነውም መጡ ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ።
17 አይተውም ስለዚህ ሕፃን የተነገረላቸውን ነገር ገለጡ።
18 የሰሙትም ሁሉ እረኞቹ በነገሩአቸው ነገር አደነቁ፤
19 ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር።
20 እረኞችም እንደ ተባለላቸው ስለ ሰሙትና ስላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና
እያከበሩ ተመለሱ።

# ምእራፍ ፪
# በአገልግሎት ድንቅ

የኢየሱስ የመወለዱ ብስራት በእርግጥም ድንቅ ነበር። የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 2 በ40ኛው ቁጥር በልጅነቱም ድንቅ እንደነበረ ይነግረናል፡

> **40 ሕፃኑም አደገ፥ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ።**

በልጅነቱም ድንቅ ነበረ። ስሙ ድንቅ መባሉ የሚያስገርም አይደለም። በኋላም፥ በአገልግሎቱ ድንቅ ነበር። ስለአገልግሎቱ ስናስብ፥ ስለመፈወሱና ነጻ ስለማውጣቱ ብቻ አይደለም የምናስብው፤ ሁሉንም አገልግሎቱን ነው የምናካትተው። *ሥራንና ቃልንም* ያጠቃልላል። ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 14፡15 እንደተናገረው፡ “*እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤*”

የኢየሱስን አገልግሎት በጥንቃቄ ልናጠናውና ልንከተለው ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ አገልግሎቱን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡ “*ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር።*” (ማቴዎስ 9፡35) የእኛም አገልግሎት እነዚህን ነገሮች ሊያካትት ይገባል።

በሉቃስ 4፡14 ላይም ስለኢየሱስ አገልግሎት ማየት እንችላለን “*ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤ ስለ እርሱም በዙሪያው ባለችው አገር ሁሉ ዝና ወጣ።*” መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ኃይል ተመለሰ ይለናል። አገልግሎቱ ድንቅ ነበር።

ስለዚህ የኢየሱስ አገልግሎት *መጀመሪያ ትምህርት*፥ ቀጥሎ *ስብከት*፥ በመጨረሻም *ፈውስን* እንደሚያካትት እናያለን።

ኢየሱስ በምድራዊ አገልግሎቱ ከምንም ነገር በበለጠ ብዙ *አስተምህሮ* አድርጓል። አራቱን ወንጌላት ሙሉ ብታነቧቸውና “እያስተማረ” ወይም “አስተማረ” የሚሉትን ቃላት ብታሰምሩባቸው ይህን ታገኛላችሁ። እንደዛም ሆኖ የኢየሱስን *ሥራዎች መሥራትን* ስናስብ፥ አብዛኛውን ጊዜ የምናስበው ድውዮችን መፈወስ አልያም ደግሞ አጋንንትን ስለማስወጣት ነው። እነዚህ ነገሮች የዚህ አካል ናቸው፥ ነገር ግን ማስተማርም ደግሞ የኢየሱስን *ሥራዎች መሥራት* ነው።

አሁን ቁጥር 32 ተመልከቱ፤ “*ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ።*” ሃሌሉያ!

ቀጥሎ ከዚሁ ምዕራፍ ውስጥ 36ኛውን ቁጥር አስተውሉ፤ “*ሁሉንም መደነቅ ያዛቸው፥ እርስ በርሳቸውም። ይህ ቃል ምንድር ነው? በሥልጣንና በኃይል ርኵሳን መናፍስትን*

*ያዝዛልና፥ ይወጡማል ብለው ተነጋገሩ።"* ይህን ያሉት ቁጥር 33 ላይ ከተደረገው በመነሳት ነው።

**ሉቃስ 4፡33-37**
**በምኵራብም የርኵስ ጋኔን መንፈስ ያደረበት ሰው ነበረ፥በታላቅ ድምፅም ጮኾ።**
**34 ተው፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄሃለሁ፥ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱሱ አለ።**
**35 ኢየሱስም። ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው። ...**

በሌላ አገላለጽ፥ ኢየሱስ "ዝም በል!" ነው ያለው። እንደዛ ነው በሰይጣን ማድረግ ያለብን -- በቃ ዝም እንዲል ንገሩት። ለሰይጣን ጨዋ ልትሆኑለት አትችሉም።

የቁጥር 35 ቀሪው ክፍል እንዲህ ይላል፡ "*ጋኔኑም በመካከላቸው ጥሎት ሳይጐዳው ከእርሱ ወጣ።"* ሰይጣኑ ከመውጣቱ በፊት የሆነ ነገር ለማሳየት ሞከረ። የመጨረሻ እድሉ እንደሆነ አውቋል፥ስለዚህ ልጁን በመካከላቸው ጣለው፥ነገር ግን ወጣ ምንምም አልጎዳውም።

**36 ሁሉንም መደነቅ ያዛቸው፥እርስ በርሳቸውም። ይህ ቃል ምንድር ነው? በሥልጣንና በኃይል ርኵሳን መናፍስትን ያዝዛልና፥ይወጡማል ብለው ተነጋገሩ።**
**37 ዝናም በዙሪያው ባለች አገር ወደ ስፍራው ሁሉ ስለ እርሱ ወጣ።**

አውነት ነው ዝናው ተስፋፍቷል (ወጥቷል።) ሰዎች ሲፈወሱና አጋንንት ሲወጡ፥ሰዎች ያወሩታል። ኢየሱስ ድንቅ ነበር፤ በአገልግሎት ድንቅ፥በሥራ ድንቅ፥እናም በቃል ድንቅ።

# ምዕራፍ ፫

# በሞቱ ድንቅ

አስባችሁታል ኢየሱስ በአገልግሎቱ ብቻ ቢያቆም ኖሮ፥ ለእኛ ምንም ድኅነት ባልኖረን ነበር? ሁሉም እዛው ያልቅ ነበር፥ ምንም አዲስ ልደት ባልኖረ ነበር።

*ያሑዋሕ ይመስገን፥ ኢየሱስ በሞቱ ድንቅ ነበር።*

ብዙ ሰዎች ስለ ኢየሱስ በሥጋና በመንፈስ መሞት ስታወሩ በትክክል አይረዱትም። "ሞት" ማለት *መኖር ማቆም* እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ውድ ወዳጆች፥ *በመጽሐፍ ቅዱስ ሞት ማለት መኖር ማቆም ማለት አይደለም።*

አዳም በመንፈስ ሲሞት ምን ተከሰተ? በሥጋው ኖሯል፥ ነገር ግን በመንፈስ ከያሑዋሕ ተለይቶ ነበር። አያችሁ፥ *መንፈሳዊ ሞት ማለት ከያሑዋሕ መለየት ማለት ነው!*

*ምክንያቱም ኢየሱስ የእኛን ቦታ ወስዷል፥ መንፈሳዊ ሞትን ልክ እንደ ሥጋ ሞትም መካፈል ነበረበት።*

ለዚህ ነው እዚህ ጋር "*አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለምን ተውኸኝ?*" ብሎ የሚጮኸው። አያችሁ፥ ያሑዋሕ ትቶት ነበር። *ያ ነው መንፈሳዊ ሞት።* ከያሑዋሕ ተለይቶ ነበር። ለምንድ ነው ያሑዋሕ የተወው? ምክንያቱም ኢየሱስ ስለእኛ ኃጢአት ሆኗል፥ ያሑዋሕ ደግሞ ኃጢአትን ሊያይ አይችልም።

ኢየሱስ ስለእኛ ኃጢአት ሆኗል! የእኔን ቦታ ወስዷል! *ለያሑዋሕ ምስጋና ይድረሰውና፥ እኔ እርሱ የሆነውን እሆን ዘንድ እርሱ እኔ የነበርሁትን ሆኗል።*

*ያን መረዳት ትችላላችሁ? ቀላል ነው---ከእናንተ የሚጠበቀው ብልህ መሆን ብቻ ነው--- አሁንም ሰዎች በዚህ ጉዳይ ላይ መጣላት ይፈልጋሉ። (እውነታው፥ ወደ ነገሩ ጫፍ ስትደርሱ፥ ያንኑ ነው የሚያምኑት፥ ካልሆነ ግን መጽሐፍ ቅዱስን አያምኑም---ከሁለት አንዱ ነው---አለበለዚያ ሊድኑ አይችሉም ነበር።)* (Actually, when you get down to brass tacks, they believe the same thing, or else they don't believe the Bible– one of the two– or they couldn't be saved.)

ብዙውን ጊዜ ሰዎች ለመከራከር ጥቂት አረፍተ ነገር (ያለቦታው) ከመልዕክቱ ውጪ ያወጣሉ። ልባቸውን ይባርከውና፥ በጣም ታዝኑላቸዋላችሁ፥ ነገር ግን ልትፈርዱባቸው አይገባም። ጭራሹኑ ትምህርት ቤት ሄዶ ለማያውቅና ማንበብ ለማይችል ትንሽ ልጅ እንደምታዝኑት ታዝኑላቸዋላችሁ። ማንበብ ስለማይችሉ አትናደዱባቸውም፥ ልክ እንደዛው፥ በመንፈስ ሕፃን በሆኑት ላይም ልትከብዱባቸው አትችሉም። ብቻ ታገሷቸው። አንዳንዶቹ አድገው በመንፈስ ሊጎለምሱ ይችላሉ። እናም ካልጎለመሱ ግን---ያው፥ ስለእነርሱ ስጋት ሊገባችሁ አይገባም። ኢየሱስን እንደ አዳኛቸው እስካመኑት ድረስ እንዲሠራ አድርገውታል።

"*አምላኬ፥ አምላኬ፥ ስለምን ተውኸኝ?*" ያሑዋሕ ኢየሱስን ለምን ተወው? ምክንያቱም ኃጢአት ሆኗልና ነው። ኢየሱስ ፈጽሞ ኃጢአት አላደረገም። ኃጢአት የሆነው የኢየሱስ ሥጋ

ነበር? አይደለም! መንፈሱ ነበር ኃጢአት የሆነው፥ ምክንያቱም ኃጢአት የሥጋ ነገር አይደለም፤ መንፈሳዊ ነገር ነው። ኃጢአት ስጋዊ ብቻ ቢሆን ኖሮ፥ ሁላችንም በሥጋ በመሞት ለራሳችን ኃጢአት መንጻት በቻልን ነበር። ነገር ግን አይደለም፥ ኃጢአት መንፈሳዊ ነው።

መስቀሉ ጋር ቆመው የነበሩት አንዳንድ ሰዎች፥ ኢየሱስ ይህን ሲል ሲሰሙ "ይህ ሰው ኤልያስን ይጠራል" አሉ።

**ማቴዎስ 27፥48-51**
**48 ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ ሮጠ፤ ሰፍነግም ይዞ ሆምጣጤ ሞላበት፥ በመቃም አድርጎ አጠጣው።**
**49 ሌሎቹ ግን፦ ተው፥ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደ ሆነ እንይ አሉ።**
**50 ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ።**
**51 እነሆም፥ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፥ ምድርም ተናወጠች፥ ዓለቶችም ተሰነጠቁ፤**

በሞቱ ድንቅ ነበር። ሃሌሉያ!

ውድ ወዳጆቼ፥ የቤተመቅደሱ መጋረጃ ከላይ ወደ ታች ለሁለት መቀደዱ ዋጋ አለው---በጣም ዋጋ አለው። በብሉይ ኪዳን ወይም በኦሪት፥ ያ መጋረጃ የቤተመቅደሱን ቅድስተ ቅዱሳን ጋርዶት ነበር። አይሁዳዊው ባለታሪክ፥ ፍሌቪየስ ጆሴፈስ፥ ሲናገር የመጋረጃው ስፋት 40 ጫማ፥ ቁመቱ 20 ጫማ፥ እንዲሁም ውፍረቱ ደግሞ 4 ኢንች ነበረ ብሏል። (Flavius Josephus, the Jewish historian) (ስፋት 12 ሜትር፤ ቁመት 6 ሜትር፤ ውፍረት 10 ሴንቲ ሜትር)

ያ ማለት በአየር ላይ 20 ጫማ ርቀት፥ አንድ መልአክ አልያም ከያሑዋሕ የተላከ ከላይ ይዞ ተርትሮታል፥ ይህም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግቢያው አሁን እንደተከፈተ ሲያሳይ ነው።

ኢየሱስ በመስቀል ከመሞቱ በፊት፥ ከሊቀ ካህኑ በቀር ማንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መግባት አይችልም፥ እናም ገብቶ ስለሕዝቡ ኃጢአት መስዋዕት ሲያቀርብ ታላቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል።

የሸኪናው ክብር---የተገለጠው የያሑዋሕ ህልውና---በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ ተዘግቶ ቆይቶ ነበር፥ ነገር ግን በስቅለቱ ቀን፥ ወደ ውጭ ወጣ።

ያሑዋሕ ከእንግዲህ ወዲህ በምድር በተሠራ ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አይኖርም፤ ያሑዋሕ አሁን በእኛ ውስጥ ይኖራል። የያሑዋሕ የሸኪናው ህልውና ክብር አሁን በልባችን ውስጥ ይኖራል! መንፈስ ቅዱስ በመንፈሳችን የያሑዋሕ ልጆች እንደሆንን ይመሰክርልናል።

# ምዕራፍ ፬

# በትንሣኤው ድንቅ

ኢየሱስ በሞቱ ድንቅ ነበር፥ እናም ያሑዋሕ ይመስገን፥ ተነስቷል። በትንሣኤው ድንቅ ነበር። ይህም ደግሞ የገና ታሪክ አካል ነው።

**ማቴዎስ 28፡1-6**
**1 በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ።**
**2 እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ።**
**3 መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ።**
**4 ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ።**

*ያም ማለት ተነጥፈው ወደቁ ማለት ነው።* (*የሞተ ሰው ቆሞ አይታችሁ አታውቁም፥ አይታችኋል*?)

**5 መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው፦ እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤**

*ለቁጥር* 6 *ተዘጋጅታችኋል*? *አስደናቂው መልእክት ይኸውላችሁ፥ ምክንያቱም “ሰሙ ድንቅ ይባላል።”*

**6 እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ።**

*የት ነው*? *በዚህ የለም*! *የምድርና የሲዖል ኃይላት ሁሉ ሊይዙት አልቻሉም። እንደ ዮሐንስ ወንጌል መሠረት፥ ማርያም እንዲህ ነው ያለችው “ጌታ ሆይ፥ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው።”* (ዮሐንስ 20፡15)

*አያችሁ፥ ብዙዎች ህያውን ከሙታን መካከል ይፈልጋሉ። ምን ያህል ሰዎች ከሞተ ነገር ላይ ህይወትን በከንቱ ፈልገዋል*? *ከሞተ ሥራ፥ ከሞተ አገልግሎት* (*ጉባኤ*)*፥ ከሞተ አምላክ ህይወትን እየፈለጉ ነው* --- *ውኃ ከሌለባቸው ጉድጓዶች።*

*በእያንዳንዱ ኃይማኖት ውስጥ ያሉት የሁሉም ሰዎች አማልክት ሞተዋል፥ ከእኛ አምላክ በስተቀር! እርሱ ህያው ነው!*

*ያሑዋሕ ይመስገን፥ ከሙታን ተነሥቷል*! *ከሙታን ተነሥቷል*! *ከሙታን ተነሥቷል*! *ሥልጣን ሁሉ አለው*!

**ማቴዎስ 28:18**
**18 ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፦ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።**

በቁጥር 18 ላይ "ኃይል" ተብሎ የተተረጎመው የግሪኩ ቃል፥ በሐዲስ ኪዳን ሙሉ "ሥልጣን" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ሁሉ ተሰጥቶኛል፥" ተብሎ ሊነበብ ይችላል። ከትንሣኤው በኋላ ወዲያውኑ ኢየሱስ በምድር ላይ ያለውን ሥልጣኑን ለቤተክርስቲያን አስተላልፏል። ሥልጣኑ በምድር ላይ የሚገለጠው በቤተክርስቲያን አማካኝነት ነው።

በቀጣዮቹ ሁለት ጥቅሶች ላይ ወደ ፊት ላካቸው፡

> **19-20 እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።**

ይህም ደግሞ በማርቆስ ወንጌል ላይ ካለው ታላቁ ተልዕኮ ጋር ይመሳሰላል።

> **ማርቆስ 16:15**
> **15 እንዲህም አላቸው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።**
> **16 ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።**
> **17 ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥**
> **18 የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።**

ከዚህ ጋር ተያይዞ ብዙ አስገራሚ ጥቅሶች አሉ፥ ነገር ግን እስቲ የኤፌሶን መልእክትን እንይ፥ ዋና ዓላማው ኢየሱስ ራስ እንደሆነ እኛ ደግሞ አካሉ ስለመሆናችን የሆነ መጽሐፍ። እስቲ ጳውሎስ በኤፌሶን ላይ የሚሰጠውን መገለጥ እንይ። አስታውሱ፥ ጳውሎስ ወንጌልን የተማረው ከሰው አይደለም።

> **ገላትያ 1:11-12**
> **11 ወንድሞች ሆይ፥ በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደ ሰው እንዳይደለ አስታውቃችኋለሁ፤**
> **12 ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም አልተማርሁትምም።**

መንፈስ ቅዱስ ለጳውሎስ ሁሉንም ነገር አስተማረው! አሁን ጳውሎስ ስለኢየሱስ ትንሣኤ የሚለውን አስተውሉ። በትንሣኤው ድንቅ ነበር።

> **ኤፌ2:1-6**
> **1 በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤**
> Eph. 2:1 And you *hath he quickened*, who were dead in trespasses and sins; (KJV) በዚህ የኪንግ ጀምስ ቨርዥን እንግሊዘኛው ትርጉም ላይ፡ *"እናንተ እርሱ ያስነሣችሁ፥* በበደላችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ፤" ይላል።
>
> "(Quickened) *መነሣት*" የሚለው ቃል፥ "ህያው መሆን" ማለት ነው። ያሑዋሕ ይመስገን፥ ከመንፈስ ሞት አስቀድመን ተነሥተናል። ህያዋን ተደርገናል። ከእነዚህ (ከሚመጡት) ቀናት በአንዱ አዲስ ሰውነት ሊኖረን ነው።

**2 በእነርሱም፥ በዚህ ዓለም እንዳለው ኑሮ፥ በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ ፈቃድ፥ በፊት ተመላለሳችሁባቸው። 3 በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።**
**4 ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥**
**5 ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥በጸጋ ድናችኋልና፥**

ያሑዋሕ ከክርስቶስ ጋር ህያዋን አደረገን። ያሑዋሕ ኢየሱስን ባስነሣው ጊዜ (ትንሣኤያችን) እንደተፈጸመ አየ። አሁን አስተውሉ፥

**6-7 በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሣን** [ይህ ብቻ አይደለም] **በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ስፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።**

ኦ፥ ለዘላለም በዚህ ላይ መስበክ እችላለሁ! አዎ፥ በትንሣኤው ድንቅ ነበር፥ ነገር ግን ታሪኩ ያ ብቻ አይደለም።

# ምዕራፍ ፫

## ዳግም በመምጣቱም ድንቅ

የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ብቻውን የያሑዋሕን እቅድ ሙሉ ምስል አይሰጠንም። የያሑዋሕ ሙሉ እቅድ ለገና በመጠቅለያ የተጠቀለለ አንድ ሕፃን ብቻ አይደለም። ያ ብቻ ቢሆን፥ ማስታወሱ ያን ያህል ጥቅም ባልኖረው ነበር። ነገር ግን ያ ብቻ አልነበረም። የያሑዋሕ ሙሉ እቅድ ምስል እንዲኖራችሁ---የኢየሱስ ልደትና ትንሣኤ---ወደ ሐዋርያት ሥራ የመጀመሪያው ምዕራፍ እንምጣ።

**ሐዋ.1:8-11**
**8 ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።**
**9 ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው።**
**10 እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኵር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤**
**11 ደግሞም። የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።**

ሃሌ ሉያ! እንደ ማጠቃለያ ወደ አንደኛ ተሰሎንቄ እንግለጥ። ያሑዋሕ ልባቸውን ይባርከውና፥ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ያላዩትን አንድ ነገር እዚህ ጋር ልንረዳ ይገባል። ውጤቱ ብዙ ሰዎች የየራሳቸውን ትናንሽ መላምቶች ሊሸጡ መሞከራቸው ነው።

ጳውሎስ የሰበከውን ወንጌል በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ እንዳገኘው መናገሩን አስታውሱ። *ስለቅዱሳን መነጠቅ ወይም መወሰድ መገለጡን የተቀበለው ጳውሎስ ብቻ ነው።*

ይህን "መነጠቅ" ወይም "መወሰድ" ("catching away" or the "Rapture") ብለን እንጠራዋለን። "መነጠቅም" መወሰድም ብላችሁ ልትጠሩት ትችላላችሁ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። እንዲሁም ይህ ክስተት "ወደ ላይ መወሰድ" ተብሎም ይጠራል። (የእንግሊዘኛው ኪንግ ጄምስ ትርጉም እንደዛ ነው የሚለው።) (የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ "እንነጠቃለን ወይም መነጠቅ" ብሎ ይጠራዋል፤ ግዕዙ ደግሞ "ንትመሠጥ" ይለዋል።)

ይህ መገለጥ ያለው ማንም ሌላ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አታገኙም። ኢየሱስ ስለዳግም ምጽአቱ ሲናገር፥ መነጠቁን አልጠቀሰም---ያልጠቀሰበት ምክንያት አለ። በቀዳሚነት ለአይሁድ ነበር እየተናገረ የነበረው፤ ለቤተክርስቲያን አልነበረም።

ስለዚህ ማቴዎስ 24ና ሉቃስ 21 ላይ አንብባችሁ፥ "እነዚህን አንብቤአለሁ ስለ መነጠቁ ምንም አያወራም፥ ስለዚህ ይህ ነገር አይሆን እንዳትሉ።"

ለምን አይሆንም? ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን እያስተማረ ወይም እየሰበከ አልነበረም፤ ለአይሁድ ነበር ሲያወራ የነበረው። ያኔ ከእርሱ ጋር አብረውት የነበሩት ደቀመዛሙርት

የጴንጤቆስጤ እለትም ነበሩ። ከላይ ኃይልን ተቀብለው ሊሰብኩ ወጡ። እናም እኛ እነርሱ የሰበኩት ሁለት እጥፍ አለን።

ኢየሱስ ወደ ሰማይ የማረጉ፥ ደመናም ከዓይናቸው ሰውሮ እንደወሰደው ይህ መልእክት በየስፍራው ሁሉ ወጣ። ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች ተገልጠው እንዲህ አሏቸው፡ "ይህ ኢየሱስ አሁን ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ተመልሶ ይመጣል።" *ይመጣል!* የቀደመችው ቤተክርስቲያን ተመልሶ እስኪመጣ እየተጠባበቀች ነበር!

በተሰሎንቄ የነበረችው ቤተክርስቲያን ተመልሶ እስኪመጣ እየጠበቀች ነበር፥ ነገር ግን በመሀከል፥ አንዳንዶቹ ሞቱ። እናም ሌሎቹ ጥያቄ ተፈጠረባቸው። ያመልጠን ይሆንን የሚል? ለምን ግራ ሊጋቡ እንደሚችሉ ልትረዱት ትችላላችሁ። ደቀመዛሙርቱ ያዩአቸው ሁለት ሰዎች በግልጽ መላእክት ነበሩ፥ እነርሱም "ይመጣል" ብለዋል።

ስለዚህ አሁን ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች እየጻፈ ነው፤

1ተሰ.4:13-18
**13 ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።** [መንፈሳቸው አይደለም ተኝቶ የነበረው፥ ሥጋቸው ነው ተኝቶ የነበረው።]
**14 ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።**
**15 በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤** [አያችሁ፥ ስለዚህ ጳውሎስ ከጌታ ዘንድ በዚህ ላይ ቃል አለው ማለት ነው።] **እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር** [ጳውሎስ እራሱ እየጠበቀው ነበር፤ ህያው ሆኖ እንደሚቀር እየጠበቀ ነበር፥ ምክንያቱም "እኛ" የሚለውን ቃል ተጠቅሟል።] **ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤**
**16 ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤**
**17 ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤** [እንነጠቃለን!] **እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።**
**18 ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።**

በሌላ ስፍራ ኢየሱስ ወደ ምድር እንደሚመጣ እናነባለን፥ ነገር ግን እዚህ ጋር የምናየው ከቅዱሳኑ ጋር ተመልሶ እንደሚመጣ ነው። ታዲያ ከእርሱ ጋር ካልሄድን እንዴት ነው ከእርሱ ጋር ተመልሰን ልንመጣ የምንችለው?

ኦክላሆማ ከተማ ውስጥ ካልነበርን እንዴት ነው ከኦክላሆማ ተመልሰን የምንመጣው? (ደብረዘይት ከተማ ውስጥ ካልነበርን እንዴት ነው ከደብረዘይት ከተማ ተመልሰን የምንመጣው?)

አዎን፥ በመጨረሻ ኢየሱስ ወደ ምድር ተመልሶ ይመጣል፥ ነገር ግን እዚህ ጋር እያወራ ያለው ይህንን አይደለም። አያችሁት?

መነጠቅ! ህያዋን ሆነን የምንቅር እንነጠቃለን! ስለመነጠቅ ወይም ስለመወሰድ (ራፕቸር) ስናወራ ይህንን ነው እያልን ያለነው። ከሁለቱ በአንዱ ልትጠሩት ትችላላችሁ።

ቁጥር 17 እንዲህ ይላል፡ “*1ተሰ.4፡17 ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።*” ከማን ጋር? በክርስቶስ አስቀድመው ከሙታን ከተነሱት ጋር።

ከእነርሱ ጋር “በደመና” እንነጠቃለን ይላል። ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል ወደ ላይ እንነጠቃለን፥ ለዘላለምም ከጌታ ጋር እንሆናለን።

በዳግም መምጣቱም ድንቅ ይሆናል፥ አይደል እንዴ?

ድንቅ ለሆነው ለያሑዋሕ እቅድ ያሑዋሕ የተመሰገነ ይሁን---ድንቅ የመዳን እቅድ!

# ኢየሱስን እንደ አዳኝ ለመቀበል

# የኃጢአተኞች ጸሎት

ውድ የሰማይ አባት፥

በኢየሱስ ስም ወደ አንተ እመጣለሁ።

ቃልህ ሲናገር፡ "… ወደ እኔ የሚመጣውን ፈጽሞ አላወጣውም" ይላል። (ዮሐ 6፡ 37) ስለዚህም ወደ ውጭ እንደማታወጣኝ አውቃለሁ፥ ነገር ግን ትቀበለኛለህና ስለዚህ አመሰግንሀለሁ።

አንተ በቃልህ እንዲህ ብለህል *"ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና።"* (ሮሜ.10:9-10) ኢየሱስ ክርስቶስ የያሑዋሕ ልጅ እንደሆነ በልቤ አምናለሁ። እኔን ለማጽደቅ ከሙታን እንደተነሣ አምናለሁ፥እናም አሁን ኢየሱስ ጌታዬ እንደሆነ አውጃለሁ።

ምክንያቱም ቃልህ እንዲህ ይላል፡ "..*ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃል*" እናም በልቤ አምናለሁ፥አሁን በክርስቶስ የያሑዋሕ ጽድቅ ሆኛለሁ። (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21) … እናም አሁን ድኛለሁ!

ጌታ ሆይ አመሰግንሃለሁ!

ፊርማ፡ ___________________________________________

ቀን፡ ____________________________________________

# ስለጸሐፊው

ኬኔት ኢ. ሄገን ያሑዋሕ በ17 ዓመት እድሜያቸው ከተዛባ ልብና ከማይፈወስ የደም ህመም በተዓምራት (በአስገራሚ ሁኔታ) ከፈወሳቸው በኋላ ለ70 ዓመታት ያህል ያሑዋሕን አገልግለዋል። ምንም እንኳን ሬቨረንድ ሄገን ወደ ቤታቸው ከጌታ ጋር ለመሆን በ2003 ቢሄዱም፥ እርሳቸው ያቋቋሙት ተልዕኮ አሁንም ድረስ ብዙዎችን በዓለም ዙሪያ መባረኩን ቀጥሏል።

የኬኔት ሄገን ተልዕኮ ስርጭቶች የሚያካትቷቸው፡ *የእምነት ቃል*፥ ነፃ ወርሀዊ መጽሔት፤ ሬማ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፤ ሬማ አሉምኒ ማህበር፤ ሬማ አለምአቀፍ የአገልጋዮች ማህበር፤ ሬማ ተያያዥነት ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት፤ እንዲሁም የሬማ የእስር ቤት አገልግሎት። የሬቨረንድ ሄገን ልጅና ባለቤቱ፥ ኬኔት ደብሊውና ሊይነት ሄገን፥ በጋራ *ሬማ ውዳሴ* የተሰኘ የቴሌቪዥን ስርጭት በሳምንት አንድ ጊዜ አላቸው፤ *ሬማ ለዛሬ*፥ በሳምንቱ ቀናት የሬድዮ ፕሮግራም፤ እንዲሁም በዓለም ዙሪያ የሚደረጉ ህያው እምነት ክሩሴዶች።

(ሬማ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ቃል (በድምጽ የተነገረ ቃል) ማለት ነው።)

**ያሑዋሕ** יהוה (𐤉𐤄𐤅𐤄) (𐤉𐤄𐤅𐤄) : በዕብራይስጥ፥ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የእሥራኤል አምላክ የሠራዊት ጌታ የኤልሻዳይ ስም ነው። ይህንም እጅግ እጅግ እጅግ የከበረ ፍጹም ቅዱስ ስም ጌታችንና አዳኛችን የያሑዋሕ ልጅና ቃል የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ መንፈሱ ለሚያፈቅሩት ልጆቹ አስታወቀው። יהוה

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን፥ አሜን።

ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com

12 11 10 09 08 15 14 13 12 11 10


*His Name Shall Be Called Wonderful*
ISBN-13: 978-0-89276-260-6
ISBN-10: 0-89276-260-8

Copyright © 1983 RHEMA Bible Church
AKA Kenneth Hagin Ministries, Inc.
All rights reserved.
Printed in USA.

*In the U.S. write:*
Kenneth Hagin Ministries
P.O. Box 50126
Tulsa, OK 74150-0126
1-888-28-FAITH
www.rhema.org

*In Canada write:*
Kenneth Hagin Ministries
P.O. Box 335, Station D
Etobicoke, Ontario
Canada, M9A 4X3
1-866-70-RHEMA
www.rhemacanada.org

The Faith Shield is a trademark of RHEMA Bible Church, AKA Kenneth Hagin Ministries, Inc., registered with the U.S. Patent and Trademark Office and therefore may not be duplicated.




## About the Author

Kenneth E. Hagin ministered for almost 70 years after God miraculously healed him of a deformed heart and an incurable blood disease at the age of 17. Even though Rev. Hagin went home to be with the Lord in 2003, the ministry he founded continues to bless multitudes around the globe.

Kenneth Hagin Ministries' outreaches include *The Word of Faith*, a free monthly magazine; RHEMA Bible Training Center; RHEMA Alumni Association; RHEMA Ministerial Association International; RHEMA Correspondence Bible School; and the RHEMA Prison Ministry. Rev. Hagin's son and daughter-in-law, Kenneth W. and Lynette Hagin, cohost *RHEMA Praise*, a weekly television broadcast; *Rhema for Today*, a weekday radio program; and *Living Faith Crusades* held around the world.

Religion/Christian Life/
General

ISBN-13: 978-0-89276-260-6
ISBN-10: 0-89276-260-8

P.O. Box 50126
Tulsa, OK 74150-0126
1-888-28-FAITH
www.rhema.org

9 780892 762606